# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
## የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ባለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ........ i

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ........ 2

ክፍል ሁለት ........ 4

የኦዲት ግኝቶች ........ 4

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ማውጣቱን በተመለከተ ........ 4

በቱሪስት አስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን በተመለከተ፣ ........ 5

የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች መለያ ዓርማ መጠቀማቸውን በተመለከተ ........ 7

የአስጎብኚዎች መመሪያ /Tour Operators Guide/ መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 9

አስጎብኚ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውን በተመለከተ ........ 11

የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 13

በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 15

በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ የላቀ አገልግሎትና ብቃት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 17

በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ስለማስገባታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማረጋገጡን በተመለከተ ........ 18

አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለማስጎብኘት አገልግሎት ብቻ ማዋላቸውን በተመለከተ ........ 20

የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና እንዲሻሻል መደረጉን በተመለከተ ........ 22

የቱሪዝም የገበያ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ ........ 24

አገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁና እንዲለሙ መደረጉን በተመለከተ ........ 26

የማስጎብኘት አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ ........ 30

ክፍል ሶስት ........ 33

መደምደሚያ ........ 33

ክፍል አራት ........ 36

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 36

አባሪ 1 ........ i

በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው እና ማስረጃ የተሰበሰበባቸው የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ዝርዝር ........ i

አባሪ 2 ........ ii

የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 294/2005 ........ ii

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቱሪዝም በዓለም ላይ ፈጣን ዕድገትን እያስመዘገቡ ካሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ አገራዊ ልማትን በመደገፍና በማፋጠን ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ቱሪዝም በውጭ ምንዛሪ ምንጭነት፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ የምርትና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማስፋፋት፣ የሥራ ስምሪት ዕድልን በመፍጠርና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
2. ኢትዮጵያ ቱሪዝምን በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች ባለቤት ናት፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የቱሪዝም ልማት ፕላን ተዘጋጅቶ ከወጣበት ከ1958 ዓ.ም ወዲህ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ተቋማት በዓይነትና በአገልግሎት ጥራት ደረጃ እድገት እያስመዘገቡ የሚያበረክቱትም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከጊዜ ወደ ጊዜ አዎንታዊ ለውጥ በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ ይህን መልካም ጅምር በማጠናከር ከቱሪዝም ልማት ህዝብን በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ በዘርፉ የተሰማሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ በጋራ በመንቀሳቀስ የታሰበው ዕድገትና ለውጥ በተፈለገው መጠንና ፍጥነት እንዲመጣ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ሀገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማግኘት እንዲቻል የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ሚና ጉልህ ድርሻ ስላለው አስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ያለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ወሳኝ ነው፡፡
4. በመሆኑም ይህን ተግባር እንዲያከናውን ሃላፊነት የተሰጠው ኢትዮጵያ ቱሪዝም ተጠሪነቱ ለባህልና ቱሪዝም መኒስቴር ተደርጎ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 ተቋቁሞ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በቅርቡ በተደረገው የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት ለውጥ ይህ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም ቱሪዝም ኢትዮጵያ በመባል ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

5. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2007/2008 ዓ.ም በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ባለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር 1/ሐ-6/225 ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በመለየትና በማጣራት ችግሮቹ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም ለመገምገም ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

6. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ባለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበት የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2011 ዓ.ም. ሶስተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ ባሉት ሶስት በጀት ዓመታት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡

7. የክትትል ኦዲቱ በዋናኛነት የተከናወነው በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሲሆን፣ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ተመርጠው ከታዩ የመንግስት ተቋማት፡- በቱሪዝም ኢትዮጵያ፣ በጉምሩክ ኮሚሽን፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም

በቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንት የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች (በብሔራዊ አስጎብኚ ኃ/የተ/የግ ማህበር፣ በያማ ኢትዮጵያ ቱርስ አስጎብኚ እና ጉዞ፣ በጋላክሲ ኤክስፕረስ ሰርቨስስ ኃ/የተ/የግ ማህበር፣ በቤጋ የማስጎብኘት አገልግሎት፣ በክብራን ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ በሰርቲን ሰንስ አስጎብኚ፣ በሰንራይዝ አስጎብኚና ጉዞ እና በአፍሮ ግሎባል አስጎብኚ) የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክትትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

8. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲት ግኝቱ ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ያዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ማውጣቱን በተመለከተ

9. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ቱሪስቶች እንደፍላጎታቸው መገልገል እንዲችሉ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ እንዳላወጣ ተገኝቶ ነበር፡፡

11. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ቱሪስቶች እንደፍላጎታቸው መገልገል እንዲችሉ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ሊያወጣና በወጣው ደረጃ መሰረት ድርጅቶቹን እየመዘነ ደረጃ ሊሰጥ እንዲሁም በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት እስከ ግንቦት 13/2010 ዓ.ም. ድረስ ያሉትን ክፍተቶች ፈትሾ ቱሪስቶች ከአስጎብኚ ድርጅቶች የሚያገኙዋቸውን አገልግሎቶች ጥራት ለማሳደግ እንዲቻል አስጎብኚ ድርጅቶችን በደረጃ ለመመደብ የሚያስችል ረቂቅ መስፈርት የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ ለባለድርሻ አካላት አቅርቦ ግብአቶችን በማሰባሰብና በማዳበር ስታንዳርዱን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

13. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-

14. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ቱሪስቶች እንደፍላጎታቸው መገልገል እንዲችሉ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ እንዳልወጣ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከብሄራዊ አስጎብኚ ኃ/የተ/የግ ማህበር፣ ከያማ ኢትዮጵያ ቱርስ አስጎብኚ እና ጉዞ፣ ከጋላክሲ ኤክስፕረስ ሰርቨስስ ኃ/የተ/የግ

ማህበር፣ ከቤጋ የማስጎብኘት አገልግሎት፣ ከክብራን ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ከሰርቲን ሰንስ አስጎብኚ፣ ከሰንራይዝ አስጎብኚና ጉዞ እና ከአፍሮ ግሎባል አስጎብኚ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

15. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ረቂቅ መመዘኛ ስታንዳርድ እንደተዘጋጀ እና ስታንደርዱን ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ማጸደቅ እንደሚቀረው ገልጸው እስካሁን የአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ አለመውጣቱን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በአዲሱ አዋጅ 1097/2010 ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ የማውጣት ስራ ለቱሪዝም ኢትዮጵያ መሰጠቱን እና አዋጁ እንዲሻሻል ጥያቄ ማቅረባቸውን እንዲሁም ለአንድ አመት ከቱሪዝም ኢትዮጵያ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም አዋጁ እስከሚሻሻል ስራውን መረከባቸውን ገልጸዋል፡፡

16. ለቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ባለመውጣቱ ቱሪስቶች የሚፈልጉትን አገልግሎት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዳያገኙ፣ የተሻለ አገልግሎት የሚሰጡትን ድርጅቶች የተሻለ ደረጃ እንዳይኖራቸው፣ አመቺ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዳይሰፍን፣ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ድርጅቶች የተሻለ ደረጃ ለማግኘት እንዳይተጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በቱሪስት አስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን በተመለከተ፣

17. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

18. በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው አስጎብኚ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች እና ያላቸውን የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግቢ በአካል ቀርበው እንዲታዩ በማድረግ ሲሆን፣ ድርጅቶቹ ያቀረቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ትክክለኛነት (ለምሳሌ፡ የሚፈለጉት ባለሙያዎች በእርግጥ እንዳሉ፣ የድርጅቶቹ የቢሮ ሁኔታ፣ የቢሮ ቁሳቁሶች፣ ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔት፣ ለማስጎብኘት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ

የመስክ ቁሳቁሶች የመሳሰሉት) ስለመሟላታቸው ድርጅቶቹ ባሉበት በአካል በመሄድ እንደማይረጋገጥ፣

19. እንዲሁም የባለሙያዎቹ የሙያ ብቃት በየጊዜው እንደማይረጋገጥ፣ በናሙና ከተመረጡ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ድርጅቶቹ ያላቸውን ንብረቶች እና ተሽከርካሪዎች እንጂ ከማስጎብኘት አንጻር ቱሪስቶች በከፈሉት መጠን አርኪ አገልግሎት ስለማግኘታቸው፣ በድርጅቶቹ ላይ የሚታየው የእድገት ለውጥ እና ለቱሪዝም ዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለመለካት የሚያስችል አለመሆኑን፣ በተጨማሪም እንደ መስፈርት የተቀመጡት እና አስጎብኚ ድርጅቶቹ በጽሁፍ ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛነትን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ተገኝቶ እንደማያረጋገጥ ለመረዳት መቻሉን በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡
20. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚሰጥበት ወቅት የተቀመጠውን መስፈርት በጽሁፍ ማስረጃ የሚቀርበውን ሁሉ በአካል የሚያረጋግጥበት እና ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ ለማሳደስ የቀረቡት ባለሙያዎች፣ ግብአቶች እና ቁሳቁሶች በሙሉ መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡
21. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት ከአስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ማረጋገጥ ጋር ተያይዞ ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶች ተለይተው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን፣ ከእነዚህ መካከል አዲስ የተከፈቱ ድርጅቶችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በአካል ተገኝቶ የሚገመገሙበት ስርዓት መዘርጋቱን፣ በሚኒስቴሩ የሚለጠፉ የተሽከርካሪ ማረጋገጫ/ቦሎዎች በተመለከተ ከክልሎች ጋር ያለውን ቅንጅት በማጠናከር የክትትል ስርዓት መፈጠሩን፣ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው ድርጅቶችን መረጃ በተደራጀ መልኩ በጥራት የሚያዙበት ስርዓት መዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡
22. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-
23. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት

ምላሽ የብቃት ማረጋገጫ በመጀመሪያ ወደ ስራው ሲገቡ ከሚንስቴር መ/ቤቱ ማግኘታቸውን እና በየአመቱ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት የሚደረግበት አሰራር ቢኖርም ከ2008 ዓ.ም በኋላ ግን የብቃት ማረጋገጫ እድሳት መደረጉ መቆሙን ገልጸዋል፡፡

24. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የብቃት ማረጋገጥ በማስረጃዎች በመደገፍ ይሰጥ እንደነበር እና ከኦዲት ግኝቱ በኋላ በአካል በመገምገም መስፈርቱ መሟላቱን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት በየአመቱ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡
25. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት የአስጎብኚ ድርጅቶች መረጃ ለማየት እንደተቻለው የብቃት ማረጋገጫ እድሳት በየአመቱ ወጥነት ባለው መልኩ እንደማይከናወን ታውቋል፡፡
26. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት በወጣው የመመዘኛ መስፈርት በትክክል የድርጅቶቹን ብቃት አለመረጋገጡ አመቺ እና ጥራት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዳይሰፍን፣ ዝቅተኛ አገልግሎት የሚሰጡት ድርጅቶች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እንዳያደርጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች መለያ ዓርማ መጠቀማቸውን በተመለከተ

27. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤
28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉት የየድርጅቶቹን ዓርማ መጠንን በተመለከተ ስታንደርድ እንዳላወጣ እና ድርጅቶቹም ዓርማቸውን ለማስጎብኘት በሚጠቀሚቸው ተሽከርካሪዎች ላይ መለጠፋቸውንና አለመለጠፋቸውን እንደማይከታተል፣
29. እንዲሁም በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቱሪስት ተሽከሪካሪዎች አርማ የሚዘጋጀው በራሳቸው በድርጅቶቹ መሆኑንና ድርጅቶቹም

አርማውን በሚፈልጉት ዓይነትና መጠን ቱሪስቶች ከሌሎች ድርጅቶች እንዲለዩዋቸው በማድረግ የሚያሰሩት መሆኑን፣ በተጨማሪም ተሽከርካሪዎቹ በስራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙበት ወቅት በብቃት ማረጋገጫው መሰረት እየሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቁጥጥር ሥራ እየተከናወነ እንዳልሆነ ተገኝቶ ነበር፡፡

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የየድርጅታቸውን ዓርማ በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉበት ሥርኣት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል፣ እንዲሁም የተሽከርካሪዎች ዓርማ መጠንን ስታንደርድ ሊያወጣ እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት በአስጎብኚነት ዘርፍ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ለተሰማሩበት የስራ መስክ ተስማሚ እና የቱሪስቶችን ምቾትና ደህንነት በአግባቡ የሚጠብቁ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ስራ ከክልሎች ጋር በቅንጅት በመከናወን ላይ መሆኑን እና የሚኒስቴሩ ልዩ መለያ ያልተለጠፈባቸው ተሽከርካሪዎች በየትኛውም የቱሪስት መዳረሻ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

32. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-

33. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ድርጅቶቻቸውን የሚያስተዋውቅ አርማ ስቲከሮችን በመኪና ጎን የሚለጥፉ መሆኑን፣ ነገር ግን የየድርጅቶቹን ዓርማ መጠንን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስታንደርድ እንዳላወጣ እና ድርጅቶቹም ዓርማቸውን ለማስጎብኘት በሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ላይ መለጠፋቸውንና አለመለጠፋቸውን እንደማይከታተል ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱን ቦሎ በተመለከተ አንድ አስጎብኚ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ለማድረግ ሲሄድ የሚሰጠውና እንዲለጥፍ ይደረግ እንደነበር፣ ነገር ግን አሁን የብቃት ማረጋገጫ እድሳት በመቅረቱ እንደማይለጠፍ ገልጸዋል፡፡

34. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አስጎብኚ ድርጅቶች በተሽከርካሪዎች በጎን እና በጎናቸው የየድርጅቶቹን ዓርማ መለጠፋቸው ለብቃት ማረጋገጫ እድሳት አንዱ መስፈርት መሆኑን እና በተለመደ ሁኔታ አስጎብኚ ድርጅቶች ድርጅታቸውን ለማስተዋወቅ ስቲከር እንደሚለጥፉ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የሚለጠፉ ስቲከሮችን በተመለከተ ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ስታንዳርድ አለማዘጋጀቱን ነገር ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ስቲከር እንደሚለጥፉ እንዲሁም ወደፊት ከስቲከር በተለየ በተሽከርካሪዎች ልዩ የሰሌዳ ምልክት ለማድረግ ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በትብብር ለመስራት ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

35. የቱሪስት ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሟቸው አርማዎች መጠን አንድ ወጥ ደረጃ የወጣለት አለመሆኑ፣ ድርጅቱም የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ቦሎ በቀላሉ መለየት የሚያስችል አለመሆኑ፣ ለቱሪስት አገልግሎት የተመደቡ ተሽከርካሪዎችን ቱሪስቶችም ሆኑ ህብረተሰቡ በቀላሉ እንዲለዩዋቸው የማያስችል የሚያደርግ እና በተለይ መንግስት ዘርፉን ለማበረታታት ሲል የፈቀደውን ከቀረጥ-ነጻ የገቡትን የቱሪስት ተሽከርካሪዎች ከታለመለት ዓላማ ውጭ አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማድረግን አዳጋች አድርጎታል፡፡

## የአስጎብኚዎች መመሪያ /Tour Operators Guide/ መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

36. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ መነሻ የሚያገለግል /minimum standard/ የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ በማዘጋጀት ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንዳላሰራጨ እና ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል እንዳላደረገ፣ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ እንደመነሻ የሚያገለግላቸው የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ እንዳልደረሳቸውና ድርጅቶቹም በራሳቸው የአስጎብኚ መመሪያ እንዳላዘጋጁ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚ መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ ሊያዘጋጅ እና ይህንን መሰረት በማድረግም አስጎብኚ ድርጅቶቹ የራሳቸው የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በማጎልበት አገራችንን የሚጎበኙ ቱሪስቶች የተሳካ የጉብኝት ስርዓት እንዲኖራቸው የሚያስችል ጋይድላይን በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ መሆኑን፣ በቀጣይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ከፀደቀ በኃላ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑንና ሁሉም ድርጅቶች የየራሳቸውን መመሪያ እንዲያዘጋጁ ክትትል እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

40. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚ መመሪያ /minimum standard Tour Operators Guide/ በማዘጋጀት ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንዳላሰራጨ እንዲሁም ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል እንዳላደረገ የገለፁ መሆኑ፣
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ለሚያስጎበኙ አካላት መመሪያ እንዳወጡና በመመሪያው መሰረት ፈቃድ እንደሚሰጡ፣ ነገር ግን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጣቸው መነሻ መመሪያ አለመኖሩን የገለፁ መሆኑ፣
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ የአስጎብኚ ድርጅቶች እና አስጎብኚዎቻቸው

የሚጠቀሙበትን የአስጎብኚ መመሪያ ለማዘጋጀት እንደ መነሻ የሚያገለግል መመሪያ /Minimum standard/ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልተዘጋጀ እና እንዲደርሳቸው እንዳልተደረገ ገልፃዋል፡፡

41. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የማንዋል ይዘት ያለው ጋይድ ላይን ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ጋር በመሆን ማዘጋጀታቸውን ነገር ግን ገና አለመሰራጨቱን ገልጸዋል፡፡
42. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የአስጎብኚ መመሪያ ለማዘጋጀት እንደ መነሻ የሚያገለግል መመሪያ /Minimum standard/ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደተዘጋጀ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
43. እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚ መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ባለማሰራጨቱ እንዲሁም ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ በማስጎብኘት አገልግሎት የሚሰማሩ አካላት የአገልገሎቱ ዝርዝር ተግባራት በትክክል አውቀው እንዳይንቀሳቀሱ ሊያደርግ እና ለስነ ምግባር ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## አስጎብኚ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውን በተመለከተ

44. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤
45. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲያድስ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ ስለመኖሩ እና ስለማሳደሳቸው የማያረጋግጥ መሆኑን እና በድርጅቶቹ ሪፖርት የሚደረገው የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደማይረጋገጥ፣
46. እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በውጭ ምንዛሪ እና በብር ያገኙትን ገቢ በየዓመቱ ፈቃድ በሚያድሱበት ወቅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት

እንደሚያደርጉ ነገር ግን ያስገቡትን ገቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛነቱን አጣርቶ ሳይሆን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት መስፈርት ስለሆነ ብቻ እንደሆነ ተገኝቶ ነበር፡፡

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአስገብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ስለማግኘታቸውና በየአመቱ ማሳደሳቸውን ሊያረጋግጥ እንዲሁም ድርጅቶቹ በየዓመቱ ሪፖርት የሚያደርጉት የውጭ ምንዛሪ ግኝት መጠን ትክክለኛነትን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

48. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት አስገብኚ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሬ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ስለማግኘታቸው ክትትል ለማድረግ እንዲረዳ የብቃት ማረጋገጥ ስራዎች ሲከናወኑ የውጭ ምንዛሪ ፍቃድ እንደ አንድ ቅድመ-ሁኔታ እንዲሆን የተደረገ መሆኑን፣ ነገር ግን ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሪን በተመለከተ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማደራጀት የሚያግዝ ወጥ አሰራር ለመዘርጋት ከብሔራዊ ባንክ ጋር በጋራ ለመስራት ውይይት የተደረገ ቢሆንም ስራው ሳይከናወን መቅረቱን ገልፀዋል፡፡

49. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-

50. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስገብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ሰባቱ በሰጡት ምላሽ ከብሄራዊ ባንክ ያገኙት ፈቃድ አለመኖሩን እና ክፍያዎችን በክሬዲት ካርድ ፖዝ ማሽን በመጠቀም፣ በቀጥታ በአካውንታቸው ገቢ እንዲደረግ በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስዊፍት አገልግሎት እንዲላክላቸው በማድረግ እና የውጭ ገንዘብ በካሽ ይዘው የሚመጡ ቱሪስቶችን በባንክ ዘርዝረው ገቢ እንዲያደርጉ በማድረግ ክፍያዎችን እንደሚቀበሉ ገልጸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በፊት የብቃት ማረጋገጫ እድሳት በሚደረግበት ጊዜ እንደሚጠየቁ አሁን ግን ሪፖርት እንደማይጠየቁ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ አስገብኚ ድርጅት በየአመቱም እንደማይታደስ፣ ሚንስቴር መ/ቤቱም የብቃት ማረጋገጫ በሚሰጥበት ወቅት ይህንን

ፈቃድ ጠይቆም ሆነ አረጋግጦ እንደማያውቅ እና እንደመስፈርትም እንደማይታይ ገልጸዋል፡፡

51. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአስጎብኚ ድርጅቶች ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በየወሩ ሪፖርት ለመቀበል የስራው ባህሪ እንደማይመች (ከፍተኛ ገቢ የሚኖርባቸው አምስት ወራቶች መኖራቸውን እንዲሁም ቱሪስቶች የማይመጡባቸው ወራቶች እንደሚኖሩ)፣ ነገር ግን አመታዊ ሪፖርት የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሲደረግ አስጎብኚ ድርጅቶች በባንክ ስቴትመንት አስደግፈው የሚልኩትን መረጃ እንደሚቀበሉ እና መረጃውን በቀጥታ ከብሔራዊ ባንክ ለማግኘት እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያወጡ አስጎብኚ ድርጅቶች እንደሚኖሩ ሆኖም አስጎብኚ ድርጅቶች ሙሉ ክፍያ በባንክ ላይቀበሉ እንደሚችሉና በዚህም ምክንያት ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ሊፈጠር እንደሚችል እና እነዚህን ችግሮች በሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

52. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውንና በየአመቱ ማሳደሳቸውን፣ እንዲሁም ድርጅቶቹ ያቀረቡት ሪፖርት ያገኙትን ትክክለኛ ውጭ ምንዛሪ የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ስለመሆኑ አለመረጋገጡ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ካገኙት ትርፍ ለመንግስት መክፈል የሚገባቸውን ትክክኛ ግብር መጠን ከማሳጣቱም በተጨማሪ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲጋለጥ በር ይከፍታል፡፡

## የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

53. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

54. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የድጋፍ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዳላደረገ፣ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ አስጎብኚ ድርጅቶች እና የአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የባህልና ቱሪዝም

ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ከመስጠት፣ የአለም ቱሪዝም ቀንን ከማክበር እና ከአስጎብኚ ድርጅቶች በተጠየቀ ጊዜ የድጋፍ ደብዳቤዎችን ከመጻፍ በስተቀር፣ ማህበሩ ከነበረበት ቢሮ እንዲወጣና በራሱ ተከራይቶ እንዲሰራ መደረጉ፣ የስልጠና እና ሌሎች ድጋፎችን አለማድረጉን፣ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ የድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዳላደረገ የገለፁ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

55. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት አስጎብኚ ድርጅቶች የተሰጣቸውን እውቅና ጠብቀው አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገ በመሆኑ በሚኒስቴሩ እውቅና ያገኑ ድርጅቶች ላይ ጠንካራ የቁጥጥር ስራ በማከናወን ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

56. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-

57. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረግላቸው ድጋፍ እና ክትትል አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

58. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሱፐርቪዥን ስርአት መኖሩን እና በቼክ ሊስት መሰረት ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

59. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የድጋፍና ክትትል ስራው ስለመሰራቱ የሚያስረዳ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

60. የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ ጎብኚዎች ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በሚፈልጉት ጊዜና በተፈለገው መጠን ማግኘት እንዳይችሉ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

61. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

62. ከአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች በሚገኙባቸው በክልሎች አካባቢ በቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች (ለምሳሌ፡- ክልሎች በጥቃቅንና አነስተኛ ያቋቋሚቸው ከቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የሚያስጎበኙ አካላት ያለአግባብ በየጊዜው ዋጋ መጨመር፣ ያላቸው የማስጎብኘት ብቃት አናሳ መሆን፣ ዩኒፎርም አለመኖር፣ ንፅህናን አለመጠበቅ፣ በሆቴሎች አካባቢ ለቱሪስቶች አልጋ ከተያዘ በኋላ ለሌላ ሰው ማከራየት እና ቱሪስቶች ለጉብኝት የሚከፍሉት ዋጋ መጨመር፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚደርስባቸው እንግልት እና ወከባ) በአግባቡ መልስ ማግኘት አለመቻል የመሳሰሉት ችግሮች መኖራቸውንና ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርም ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን የገለፁ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

63. ከቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት በሚኒስቴርመ/ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

64. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት በድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

65. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከ10 ዓመት በላይ የሆናቸው ተሽከርካሪዎች እንዲቀየሩ ጥያቄ እንዳቀረቡ እና መልስ እንዳልተሰጣቸው እንዲሁም የመሰረተ ልማት ችግር በመዳረሻዎች መኖሩን ነገር ግን መልስ እንዳልተሰጠበት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በቁጥር ኢቱአአ/1030/11 መስከረም 10 ቀን 2011 ዓ.ም ለባህልና ቱሪዝም ሚንስቴር በጻፉት ደብዳቤ በአዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር በየአመቱ የሚታደስ የኤርፖርት ተርሚናል መግቢያ ፈቃድ ለማህበራቸው አባላት እንዲሰጥ እገዛና ድጋፍ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም የክትትል ኦዲቱ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ፈቃድ ያለማግኘታቸውን ገልጸዋል፡፡
- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስድስቱ በሰጡት ምላሽ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅሬታ አቅርበው እንደማያውቁ የገለጹ ሲሆን፣ ሁለት አስጎብኚ ድርጅቶች ቅሬታዎችን ይዘው ቢቀርቡም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልፈታላቸው ገልጸዋል፡፡

66. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መኖሩን እንዲሁም በዚህ ስራ ክፍልም ቅሬታዎች ሲቀርቡ የሚፈቱበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡
67. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቀት ከአስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓትን የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
68. ከአስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጀቶች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዳይሰጡ እና እንዳይበረታቱ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ መጠን እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ የላቀ አገልግሎትና ብቃት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

69. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

70. በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት ማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

71. በቱሪዝም ሴክተር በተለይም በማስጎብኘት ሥራ ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙትን አካላት ዕውቅና የሚሰጥበት የማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

72. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ እና ውጤታማ ስራ ለሰሩ አካላት እውቅና ለመስጠት የሚያስችል አሰራር መመሪያ መዘጋጀቱን በዚሁም መሰረት በዘርፉ የላቀ አስተዋፅዖ ያበረከቱ አካላትን የሚበረታቱበት ዓመታዊ መድረክ ለማዘጋጀት ዕቅድ መያዙን ገልፀዋል፡፡

73. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በቱሪዝም ሴክተር በተለይም በማስጎብኘት ሥራ ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል  የተሰጠ ማበረታቻ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡
- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስድስቱ በሰጡት ምላሽ በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ

ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት ማበረታቻ ሥርዓት አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

74. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት የማበረታቻ መመሪያ እንደወጣ ነገር ግን ተግባራዊ እንዳልተደረገ ገልፀዋል፡፡

75. በቱሪዝም ሴክተር የተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የተሻለ አገልግሎት ለደንበኞቻቸው የሚሰጡ እና ለሀገርም የሚጠበቅባቸውን የውጭ ምንዛሪ መጠን የሚያስገቡ ድርጅቶች እንዳይበረታቱ ያደርጋል፡፡

## በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ስለማስገባታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማረጋገጡን በተመለከተ

76. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

77. የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ለማስገባታቸው ሳይረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እና ፈቃዳቸውም እንደሚታደስላቸው በናሙና ከታዩ የአስጎብኚ ድርጅቶች የግል ፋይል ለማወቅ ተችሎ ነበር፡፡

78. አስጎብኚ ድርጅቶች በየዓመቱ ፈቃዳቸውም ከመታደሱና የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት እንቅስቃሴያቸውን የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ስለማስገባታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያረጋግጥ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

79. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

80. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተለው ሁኔታ ተገኝቷል፡-

81. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስድስቱ በሚኒስተር መ/ቤቱ ተጠይቀው እንደማያውቁ እና ሪፖርት እንደማያቀርቡ የገለፁ ሲሆን፣ ሁለቱ ደግሞ በየዓመቱ የባንክ መግለጫ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል፡፡

82. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ አስጎብኚ ድርጅቶች መረጃ እንደታየው አንዳንድ የአስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ማረጋገጫ እና እድሳት መጠየቂያ ቅጽ ላይ የድርጅቶችን የስራ እንቅስቃሴ (ያስተናገዷቸው ቱሪስቶች ብዛት፣ የተገኘው ገቢ በውጪ ምንዛሬ፣ የተገኘው ገቢ በብር እንዲሁም የቀጣይ አመት የእቅድ መግለጫ) የተሞላ ቢሆንም አንዳንድ የአስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ማረጋገጫ እና እድሳት መጠየቂያ ቅጽ ላይ ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥያቄው አልተቀመጠም፡፡ ይህም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተከታታይነት እና ወጥነት ባለው መልኩ ሀገሪቱ ያገኘችውን የውጭ ምንዛሬ እንደማይመዘግብ እና አስጎብኚ ድርጅቶቹ ያቀረቡት የውጭ ምንዛሬ እና ገቢ ትክክለኛነትን የሚረጋገጥበት ሁኔታ አለመኖሩን ያሳያል፡፡

83. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሲደረግ አመታዊ ሪፖርት እንደሚጠይቁ እና በባንክ መግለጫ አስደግፈው ሪፖርት እንደሚያደርጉላቸው ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ በባንክ ላይፈፀሙ እንደሚችሉ እና ሳይገቡ ሊቀሩ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡ ይህንን ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠር እንደማይችል ገልፀዋል፡፡

84. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ አስጎብኚ ድርጅቶች መረጃ አልፎ አልፎ በቼክ ሊስት በተጠየቁት ላይ የተሞላ አመታዊ በውጭ ምንዛሪ የተገኘ ገቢ እና የባንክ መግለጫ እንጂ በሁሉም ድርጅቶች መረጃ ላይ አለመኖሩን ያረጋገጥን በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

85. በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ስለማስገባታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመረጋገጡ ሀገረቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ በትክክል ስለማግኘቷ ለማወቅ አያስችልም፡፡

## አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለማስጎብኘት አገልግሎት ብቻ ማዋላቸውን በተመለከተ

86. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

87. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስጎብኚ ድርጅቶች እና ግለስብ አስጎብኚዎች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለማስጎብኘት አገልግሎት ሥራ ብቻ ስለማዋላቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደረግ ተገኝቶ ነበር፡፡

88. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል ሊያደርግ እና ከተፈቀደላቸው ውጭ ሲጠቀሙ በተገኙት ላይ የዕርምት እርምጃ መወሰድ አለበት እንዲሁም የቀረጥ ነጻ መብት አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚነሱ የተለያዩ አለመግባባቶችን በፍጥነት የሚፈቱበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የማስጎብኘቱ አገልግሎት የተቀላጠፈ ሊደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት በማበረታቻነት ከቀርጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው አላማ እየዋሉ ስለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚካሄድ ገልጸዋል፡፡

90. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ለገቢዎች ኮሚሽን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ያገኙትን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት ስራ ብቻ ስለመዋሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ የገለፁ መሆኑ፣
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ

በእነሱ በኩል መኪኖቹን መቆጣጠር ከባድ እንደሆነ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረገው  ቁጥጥር የላላ እንደሆነ የገለፁ መሆኑ፣

- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፡-
    - ✓ አራቱ አስጎብኚ ድርጅቶች ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኙትን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት አገልግሎት ስራ ብቻ ስለማዋላቸው ክትትል እና ቁጥጥር እንደማያደርግ የገለፁ መሆኑን፣
    - ✓ አንድ አስጎብኚ ድርጅት ደግሞ የገቢዎች አዋጅ ላይ ለታለመለት አላማ የሚለው ትረጉም ላይ ክርክር የነበረበት መሆኑንና ሚኒስቴር መ/ቤቱም እስካሁን ትርጓሜውን ማስተከከል እንዳልቻለና አሁንም ችግር እንዳለ የገለፁ መሆኑን፣
    - ✓ ሁለቱ አስጎብኚ ድርጅቶች  ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ የገለፁ ሲሆን፣ አንድ አስጎብኚ ድርጅት ጉምሩክ ኮሚሽን እንደሚከታተል ገልጸል፡፡
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገቢዎች እና ጉምሩክ በየቅርንጫፉ ያሉ አስፈጻሚ አካላት ላይ የታለመለት አላማ በሚለው ቃል ትርጓሜ ላይ የግንዛቤ ችግር መኖሩን እና የተፈቀደው እና ያልተፈቀደው ምን እንደሆነ ግልጽ መመሪያ አለመኖሩን እንደ ምሳሌ ሀበሻ ለምን ጫንክ በሚል መኪኖች የሚታገዱበት ሁኔታ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

91. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቅንጅት እየሰሩ እንዳልሆነ እና ጉምሩክ ኮሚሽን በራሱ መንገድ እንደሚሰራ እንዲሁም ይህን ቁጥጥር የሚያደርገው የገቢዎች ኮሚሽን እንደሆነ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ መመሪያ እንደሚገልፅ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የታለመበት ዓላማ የሚል ቃል ሰዎች የተረዱበት ሁኔታ ልዩነት እንዳለው እና ህጉን ማስከበር ላይ እና አፈፃፀም ላይ ክፍተት እንዳለና ይህን ለማሻሻል ጥረት እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡

92. አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኙትን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲያውሉ በመቀናጀትና በመግባባት የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ አገሪቱ ከዘርፉ አገኘዋለሁ ብላ በማበረታቻ መልክ የተወችውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ገቢ ዓላማውን እንዳይመታ የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና እንዲሻሻል መደረጉን በተመለከተ

93. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

94. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ሥራ የተጀመረ ቢሆንም የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት አለመዘርጋቱ እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት አለመሰራጨቱ ተገኝቶ ነበር፡፡ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ለታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ዘርግቶ የተቀላጠፈ መረጃ (የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች፣ ከቱሪዝም አንጻር የገበያው ፍላጎት፣ ወዘተ...) ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንደማያደርስ የገለጹ መሆኑን፣ እንዲሁም የአስጎብኚ ድርጅቶቹንም የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘና እና በየጊዜው ወቅታዊ ስለመደረጉና ተፈላጊውን መረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ አለመለካቸውን እንደማይከታተል ታውቆ ነበር፡፡

95. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት በመዘርጋት እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

96. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት የዘርፉን ልዩ ልዩ መረጃዎች ወቅታዊ የማድረግና በተሟላ መልክ የማሰባሰብ እና የማደራጀት ስራዎች

የተከናወኑ መሆኑን፣ በተጨማሪም የሀገሪቱን ዘርፈ ብዙ የቱሪዝም ሀብቶችን የሚያስተዋውቁ የተለያዩ የፕሮሞሽን ማቴሪያሎች ተዘጋጅተው በልዩ ልዩ መንገዶች በውጭ እና በሀገር ውስጥ ተደራሽ መደረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

97. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ለአዲስ አበባ መስተዳድር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት ብዙም እንዳልተሄደበት የገለፁ መሆኑ፣
- ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የመረጃ መለዋወጥ ችግር መኖሩን እና በአለም አቀፍ ደረጃ ቱሪስቶችን ወደ አገሪቱ ለመሳብ እንዲረዳ አገሪቱ ያላትን የባህልና ቱሪዝም መስህቦች የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማሰራጨት የቱሪዝም ኢትዮጵያ ስራ ቢሆንም ስራው እየተሰራ እንዳልሆነ በተጨማሪ የመረጃ አሰባሰብ ላይ ትልቅ ችግር እንዳለ የገለፁ መሆኑ፣
- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ አራቱ ድርጅቶች በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ሥራ የተጀመረ ቢሆንም የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት አለመኖሩን የገለፁ መሆኑ፣
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ሀገሪቱን ለማስተዋወቅ እየተሰራ አለመሆኑን እንዲሁም መረጃ የማደራጀት ስራ አለመሰራቱን እና በሀገሪቱ የቱሪዝም መረጃ ቋት አለመኖሩን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ (የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች፣ ከቱሪዝም አንጻር የገበያው ፍላጎት፣ ወዘተ...) ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንደማያደርስ ገልጸዋል፡፡

98. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሀገርን የማስተዋወቅ ስራ በበቂ ሁኔታ አለመሰራቱን፣ የቱሪዝም አለም አቀፍ መድረኮች ላይ መሳተፍ የቀረበት ሁኔታ መኖሩን፣ ሀገርን የማስተዋወቅ እና የገበያ ማፈላለግ ስራ የቱሪዝም ኢትዮጵያ ሲሆን ባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቁጥጥር ስራውን መስራቱ የአሰራር ክፍተቶች መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

99. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ቱሪዝም ኢትዮጵያ እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም ድረስ የባህልና ቱሪዝም ተጠሪ ተቋም በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን አለመከታተሉ አግባብ አይደለም፡፡ እንዲሁም ከህዳር 2011 በኋላ ቱሪዝም ኢትዮጵያ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ቢሆንም የቱሪስት መዳረሻ ልማት፣ የገበያ ማፈላለግ፣ ገጽታ የመገንባት እና የመሳሰሉት ስራዎች በአስጎብኚ ድርጅቶች ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ አስተዋጾ ስለሚኖረው በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡ (የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት በአዋጅ 916/2008 ለባህል እና ቱሪዝም ሚንስቴር እንዲሁም በአዲሱ አዋጅ 1097/2011 ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ሆኖ ቱሪዝም ኢትዮጵያ ተብሎ ሲቋቋም ተግባር እና ኋላፊነቱ በተመለከተ አባሪ 2 ተያይዟል፡፡)

100. የክትትል ኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከቱሪዝም ኢትዮጵያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ቢያደርግም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

101. የአገሪቱ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማዕከል ደረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት አለመዘርጋቱ እና መረጃዎቹን በመጠቀም ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ባለመድረሱና ባለመተዋወቁ ሀገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች በአግባቡ የማስተዋወቅ እና የማሳወቅ ስራ እንዳይሰራ የመረጃ እጥረት ክፍተት የሚፈጥር እና ከዘርፉ መገኘት የሚገባውን ያህል ጥቅም እንዳይገኝ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## የቱሪዝም የገበያ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ

102. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

103. የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ያልተሰራ መሆኑ፣ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና

ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቱሪዝም ገበያ የማስተዋወቅ ስራን ከሚያግዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከርና ወቅታዊ የገበያ ጥናት ስራዎችን በቅንጅት በመስራት የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገፅታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ በዋናነት የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት እንደተጠበቀው እንዳልተሰራ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ተቆጣጣሪ አካል እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት የቱሪዝም የገበያ ማስፋፋት ስራ መስራቱን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባ እንደነበር ተገኝቶ ነበር፡፡

104. በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ስለመሰራቱ የክትትልና ቁጥጥር ስራ እንዲሰራ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

105. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት ሀገሪቱን በአለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ለማስተዋወቅ እና ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

106. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- የአዲስ አበባ መስተዳድር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ቀን ከአስጎብኚ ድርጅቶች በጋራ በማክበር ገፅታ ማስተዋወቅ ስራ እንደሚሰሩ ነገር ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተፈጠረ የገበያ ትስስር አለመኖሩ እና ወቅታዊ የገበያ ጥናት ስራዎች አለመሰራታቸው የገለፁ መሆኑ፣
- ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ይህ ስራ እንደ ሀገር እንዳልተሰራ የገለፁ መሆኑ፣
- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ሰባቱ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በማስተዋወቅ

ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር እንዳልፈጠረ ሲገልጹ፣ አንዱ በተለያዩ የንግድ ትሪኢት ላይ በመሳተፍ እንደሚያስተዋውቁ የገለፀ መሆኑ፣

- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ሀገሪቱ አለም ላይ የማይገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ቢኖሯትም ቱሪስቶች ሲመጡ የሚያዩት ነገር ገጽታችንን ያበላሸ መሆኑን ለምሳሌ መዳረሻዎች አካባቢ የልመና፣ የስርቆት፣ ላልሰሩት ስራ ብዙ ክፍያ መጠየቅ እንዲሁም በቅርብ ጊዜ በደቡብ ክልል ቱስቶችን የመዝረፍ ሁኔታ ተፈጥሮ በህግ አካላት ድጋፍ ያልተገኘበት ሁኔታ እንደነበረ እንዲሁም ቱሪስቶች በማህበራዊ ሚዲያ (ቱሪስት ጋይድ) የገጠማቸውን ሲጽፉ የሚያስተባብል ተቋም አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

107. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህ ስራ የቱሪዝም ኢትዮጵያ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

108. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የቱሪዝም ኢትዮጵያ እስከ ሕዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደ ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

109. የክትትል ኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከቱሪዝም ኢትዮጵያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ቢያደርግም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

110. የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ባለመሰራቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በሚፈለገው መጠን እንዳያድጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ለማሳደግ እንዳትችል እንቅፋት ሆኗል፡፡

## አገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁና እንዲለሙ መደረጉን በተመለከተ

111. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገሪቱ ያሏት ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ በአገሪቱ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቱሪስት መስህቦች ለቱሪዝም እና ለቱሪስቶች አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማቶች እንዲሟላላቸው አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣ የአዲስ አበባ ከተማ

መስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አብዛኛዎቹ (ለምሳሌ፡ የሶፍ ዑመር ዋሻ፣ መልካ ቁንጡሬ፣ ወዘተ.) አገሪቱ ያላት የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረት ልማት አውታሮች እንዲሟሉላቸው በማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በቂ የገበያ ትስስር ስራ እንዳልተሰራ ተገኝቶ ነበር፡፡

113. ሀገሪቱ ያላት ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት የጎብኚዎች ቁጥር የሚያድግበትን ሁኔታ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ እንዲደረግ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት በሀገራችን የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን በዘላቂነት በማልማት ለቱሪስቶች ምቹ ለማድረግ የሚያግዝ የመዳረሻ ልማት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በረቂቅ ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በቀጣይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ግብአቶችን በማሰባሰብ እና በማዳበር ተግባራዊ እንደሚደረግ የሚጠበቅ መሆኑን፣ የሀገራችንን ገጽታ በአለም አቀፍ ደረጃ ለመገንባት የሚያስችሉ የተለያዩ የገበያ ፕሮሞሽን ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙና በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በሚካሄዱ የቱሪዝም ንግድ ትርኢቶች እና የመንገድ ላይ ትርኢቶች ውጤታማ ተሳትፎ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

115. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ አምስቱ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገሪቱ ያላትን ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ በአገሪቱ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቱሪስት መስህቦች ለቱሪዝም እና ለቱሪስቶች አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ እንዳላደረገ ሲገልጹ፣ አንድ

አስጎብኚ ድርጅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከወረት የዘለለ የጠበቀ ግንኙነት እንደሌለው የገለፀ መሆኑ፣ አንድ አስጎብኚ ድርጅት ደግሞ ስራው የቱሪዝም ኢትዮጵያ እንደሆነ እና ቀሪው አንድ አስጎብኚ ድርጅት መረጃው እንደሌለው ገልጿል፡፡

- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የቱሪስት መዳረሻዎች የመንገድ፣ የመብራት፣ ሽንት ቤት እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎት አለመኖሩን ገልጸው ለምሳሌ **World Travel** & Tourism Council (WTTC) በ2018 ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ በመዳረሻ መሰረተ ልማቶች ከአለም ወደ መጨረሻ አካባቢ መሆኗን እና በሀገር ደረጃ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ትኩረት እንዳልተሰጠው ገልጸዋል፡፡
- ሁለት በኢትዮጵያ በጥቅምት 2018 ለአንድ ወር ጉብኝት ያደረጉ አውስትራሊያዊያን ቱሪስቶች በጉብኝታቸው ወቅት ያዩትን አስተያየት ለባህል እና ቱሪዝም ሚንስቴር፣ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት እና ለኢትዮጵያ አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በጻፉት ኢሜል በጉብኝታቸው ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ሰሜን ተራሮች፣ የሱሉልታ ኮረብታ፣ የጅማ ስምጥ ሸለቆ፣ ደብረ ሊባኖስ፣ አንኮበር፣ አዋሽ፣ ላንጋኖ ሀይቅ፣ አዋሳ ሀይቅ፣ ያቤሎ ነገሌ እና የባሌ ተራሮችን ማየታቸውን እና የሚከተሉት ችግሮች እንዳሉ ገልጸዋል፡-
    - ➢ ብሄራዊ ፓርኮች እና ጥብቅ ቦታዎች እየጠፉ መሆናቸውን ለምሳሌ ብሄራዊ ፓርኮችን ለግጦሽ እና ለእርሻ የመመንጠር፣ የፓርኮች መመናመን እና የውሃ ምንጮች መጎዳት በከፍተኛ ሁኔታ የዱር እንስሳት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን፣
    - ➢ በደቡብ አካባቢዎች ነገሌ እና ያቤሎ የጎሳ ግጭቶች እንዲሁም በተደራጁ ወጣት ወንድ ሌቦች ቱሪስቶችን የመዝረፍ እና የማጥቃት ሁኔታ ቢኖርም በአካባቢው ያሉ የህግ አካላት መፍትሄ ያለመስጠት፣
    - ➢ በቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ባሉ ነዋሪዎች እና ህጻናት ከፍተኛ ልመና መኖሩ እንዲሁም ዝርፊያ የሚፈጸም መሆኑን ገልጸው

አፋጣኝ መፍትሄዎች በዱር እንስሳት እና መኖሪያዎቻቸው ላይ የጥበቃ ስራ ካልተሰራ ከ3-7 አመት ውስጥ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች ሊጠፉ እንደሚችሉ እንዲሁም በጎሳ ግጭቶች እና ለቱሪስቶች በሚታዩ ባህሪዎች ላይ አፋጣኝ መሻሻል ከሌለ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንደሚጎዳ የገለፁ መሆኑን፣

- የ2009 ዓ.ም የበጀት ዓመት የሴክተር ዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ በአለም ተፈጥሮ ቅርስ የተመዘገበ ብቸኛው ብሄራዊ ፓርክ ቢሆንም በውስጡ የያዛቸው የዱር እንስሳቶቹ እየተመናመኑ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው በመሆኑ ዩኔስኮ ፓርኩን በአለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስ አደጋ መዝገብ ውስጥ በመመዝገብ የአይ ዩ ሲ ኤን ገምጋሚ ቡድን በመላክ ከተገመገመ በኋላ ፓርኩን ከአደጋ መዝገብ ለማሰረዝ የገምጋሚ ቡድኑ ያስቀመጠውን መስፈርቶችን እንዲያሟላ መጠየቁ ተገልጸል፡፡

116. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መዳረሻ ማልማት ስራ የቱሪዝም ኢትዮጵያ ስራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

117. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የቱሪዝም ኢትዮጵያ እስከ ሕዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደ ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

118. የክትትል ኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከቱሪዝም ኢትዮጵያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ቢያደርግም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

119. አገሪቱ ያላትን ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ባለመደረጉ ሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል፡፡ እንዲሁም የቱሪስት መዳረሻዎች መሰረተ ልማት አለመሟላቱ፣ በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶች እና የተፈጠሮ ቅርሶች በቂ ጥበቃ አለመኖሩ ሀገሪቱ ከቱሪዝም የምታገኘውን ገቢ ዘላቂነት እንዳይኖረው ያደርገዋል፡፡

## የማስጎብኘት አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ

120. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

121. የማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

122. የቱሪስት ማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው መሰረት ከማስጎብኘት ስራ ጋር በተገናኘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ከህዝብ ክንፍ ጋር በቅንጅት የተለያዩ ስራዎች በመከናወን ላይ እንደሚገኙ፣ በዘርፉ ከተሰማሩ የሙያና የቢዝነስ ማህበራት ጋር የእቅድ ትስስር የተካሄደ መሆኑንና ተግባራትን በጋራ የመፈጸም እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን በተጨማሪም ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተገናኘ የሚታዩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በከፍተኛ አመራር ደረጃ ውይይት በማድረግ ችግሮቹ እንዲቃለሉ እንደተደረጉ ገልጸዋል፡፡

124. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ለጉምሩክ ኮሚሽን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ተቀናጅቶ የመስራት ችግር እንዳለ ገልፀዋል፡፡

- ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚያስችል ቱሪዝም ካውንስል በአገር ደረጃ የተጀመረ ነገር እንደነበረና የተጠናከረ እንዳልሆነ እና ተናቦ የመስራት ችግር እንዳለ ገልፀዋል፡፡
- በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ከተያዘ ስምንት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ አምስቱ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን ሲገልጹ፣ ሁለቱ አስጎብኚ ድርጅቶች ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር ግንኙነት እንዳለ የገለፁ መሆኑን፣ አንዱ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር እንደሚሰራና ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በተወሰነ ደረጃ በቅንጅት እንደሚሰራና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር ግን ቅንጅታዊ አሰራር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን ለምሳሌ ቱሪስቶች ሲመጡ አየር መንገድ ውስጥ አስጎብኚዎች ገብተው እንዲቀበሉ እንደማይፈቀድ በዚህም ቱሪስቶች እንደ መጡ የሚቀበላቸው አስጎብኚ እንደሌለ እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በየኢምባሲው ሀገርን የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራ ቢደረግ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በቅንጅት ቢሰራ፣ ኢሚግሬሽን ከሆቴሎች እና መዳረሻዎች ጋር አብሮ ቢሰራ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

125. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተቀናጅቶ የመስራት ችግር እንዳለ ለምሳሌ አየር መንገድ ውስጥ ከደህንነት አንፃር አስጎብኚ ውስጥ ገብቶ መቀበል እንደማይችል ገልፀዋል፡፡ የቱሪዝም ካውንስል ተቋቁሞ እንደነበር ይሁን እንጂ ብዙም ውጤታማ ስራ እየሰራ እንዳልሆነ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ

በተናጠል ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በእያንዳንዱ ስራ የሚገናኙበት ሁኔታ እንዳለ አክለው ገልፀዋል፡፡

126. ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አለመኖሩ የማስኀብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በአፋጣኝ ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት እንቅፋት ሆኗል፡፡

Office of the Federal Auditor General

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

127. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ብቃት ባለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎች መኖራቸውን እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ቱሪስቶች ከአስጎብኚ ድርጅቶች የሚያገኙዋቸውን አገልግሎቶች ጥራት ለማሳደግ እንዲቻል አስጎብኚ ድርጅቶችን በደረጃ ለመመደብ የሚያስችል ረቂቅ መስፈርት የተዘጋጀ መሆኑ
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡ ተሽከርካሪዎች የተሟላ መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግቦ መያዙ፣
- ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ እና ውጤታማ ስራ ለሰሩ አካላት እውቅና ለመስጠት የሚያስችል አሰራር መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑ

### 3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው አስጎብኚ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ትክክለኛቱ ሳያረጋገጥ መሆኑ፣
- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉት የየድርጅታቸው ዓርማ መጠን ስታንደርድ ያላወጣ እና መለጠፋቸውንም የማይከታተል መሆኑ፣

- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚዎች መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ ያልተዘጋጀ መሆኑን እና ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣
- ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲያድስ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ስለማግኘታቸውና በየአመቱ ስለማሳደሳቸው እና በየዓመቱ ሪፖርት የሚያደርጉት የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ከቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት የቅሬታና የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ለማስገባታቸው ሳይረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው እና ፈቃዳቸውም የሚታደስላቸው መሆኑ፣
- የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋል አለመዋላቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት በመዘርጋት እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት የማያሰራጭ መሆኑ፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- ሀገሪቱ ያላት አብዛኛዎቹ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባባር ያልተደረገ መሆኑ፣

❖ የቱሪስት ማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

128. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

129. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍሌ ሦስት ሊይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዱት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑ ነጥቦች ላይ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

130. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከለና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዱት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁለም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡ በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና የታዩት ስምንት አስጎብኝ ድርጅቶች፣እና አራት ባለድርሻ አካላት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1

# በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው እና ማስረጃ የተሰበሰበባቸው የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ዝርዝር

፩. በናሙና ለተመረጡ አስጎብኚ ድርጅቶች

1. ብሔራዊ አስጎብኚ ኃ/የተ/የግ ማህበር፣
2. ያማ ኢትዮጵያ ቱርስ አስጎብኚ እና ጉዞ፣
3. ጋላክሲ ኤክስፕረስ ሰርቨስስ ኃ/የተ/የግ ማህበር፣
4. ቤጋ የማስጎብኘት አገልግሎት፣
5. ክብራን ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣
6. ሰርቲን ሰንስ አስጎብኚ፣
7. ሰንራይዝ አስጎብኚና ጉዞ እና
8. አፍሮ ግሎባል አስጎብኚ) ኤም ዲ አስጎብኚ ድርጅት /MD Tour Services/

# አባሪ 2

## የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 294/2005

የቱሪዝም ኢንፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የምክር ቤቱ ሴክረተሪያት ሆኖ የማገልገል
2. የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀት እና በመምራት የሀገሪቱን የቱሪዝም ሀብቶች በውጭ ሀገር እና በሀገር ውስጥ የማስተዋወቅ
3. የሀገሪቱ የቱሪዝም መስህቦች እና አገልግሎቶች መረጃ ማእከላትን በመግቢያ በሮች እና በማእከል የማደራጀት፣ የማስተባበር እና የመምራት
4. የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርት እና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽ እና በየጊዜው በማሻሻል በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ
5. የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎች እና የጥናት አይነቶችን የመለየት፣ የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀት እና የማሰራጨት
6. የቱ ሪዝም ልማት እና ማርኬቲንግ አገልግሎት ክፍተት በመለየት የሥልጠና ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት
7. ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነት እና ትብብር የመፍጠር
8. ነባር እና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣ የግል ባለ ሀብቶች በልማቱ እንዲሳተፉ የማበረታታት
9. አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ጥናት እና ምርምሮች የማካሄድ
10. ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማእቀፎች በማዘጋጀት ስራ ላይ የማዋል
11. በውጭ ሀገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግንኙነት የመመስረት
12. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስ እና የመከሰስ

13.አላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን

- ቱሪዝም ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ተቋቁሟልየሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትየሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፡

ለ.ሥልጣንና ተግባርን ለማስፈፀም እንድያስችላቸው የቱሪዝም ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተድራል፣

ሐ. የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ ስልት ነድፎ ይተገብራል፣ መስህቦችና የአገልግሎት መረጃ ማዕከላትን በመግቢያ በሮችና በማዕከል ያደረጃል፣ያስተባብራል፣ይመራል፣

መ. የአገሪቱ የቱሪስት መስክቦች በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት በዓለም አቀፍ ቅርስነት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሠ. የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶችን መለያ በመቅረፅና በየጊዜውበማሻሻል በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

ረ. የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎችንና የጥናት ዓይኖቶችን ይለያል፣ ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣

ሰ. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈፃሚነቱ ይቆጣጠራል፣

ሸ. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እንዲስፋፋ፣ የየአካባቢው ማህበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል

ቀ. የቱሪዝም ልማትን ማርኬቲንግ የአገልግሎት ክፍተት በመለየት የስልጠና ፍላጎት የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

በ. ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር ይፈጥራል፣

ተ. የቱሪዝም ዘርፉን እድገት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያከናውናል፣ በሚመለከተው አካ ሲፀድቅ ይተገብራል፣

ቸ. ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የግል ባለሀብቶች በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፣

ኀ. የሰመረ የቱሪዝም አገልግሎት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በስራ ላይ ያውላል፣ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፣

ነ. በውጭ አገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግኑኝነት ይመሰርታል